# 1. መልክእ

ገዛኸኝ ጌታቸው

## 1.1 መልክእ ምንድን ነው?

«መልክእ» የግእዝ ቃል ሲሆን «ለክአ» ከሚለው ግስ የወጣ ነው። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ «ለክአ» ማለት «ጣፈ፣ ፀተመ፣ ሣለ መሰለ፤ መልክ አወጣ፤ በቀለም በቅርጽ» /1948፣ 565/ ነው በማለት መልክእን በቁሙ፣ መልክ፣ ገጽ፣ የፊት ቅርጽ፣ ሥዕል ምስል፣ ልክ ያለው በልክ የተሠራ» /1948፣ 566/ በማለት ይፈቱታል። ስለዚህ መልክእ በጥሬ ፍችው ለግዙፍ ነገር ማለት ለሰዎች ወይም ለእንስሳት የሚነገር ይሆናል፤ ብዙ ቁጥሩም መልክእት ነው። ሌላውና ለዚህ ጽሁፍ ተስማሚው የቃል ፍቺ ለግእዝ የሥነ ግጥም ዓይነት የተሰጠው ስም መሆኑ ነው። በዚህ ረገድ ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም ሆነ ከዘመናዊ ምሁራን ከተሰጡት መካከል አሟልቶ ያልያዘው ነገር ያለ ይመስለኛል። ከሁለቱም ክፍሎች ሁለት ሁለት ፍቺዎችን እንመልከት።

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ/1948፣ 556/ መልክእ የድርሰት ስም፣ የመልክ ውሳኔና መዝሙር ከራስ ጠጉር እስከ እግር ጥፍር የሚቆጥር ይሉታል። ይህ ፍቺ በብዙ የቤተ ክርስቲያንም ሆነ ዘመናዊ ሊቃውንት ተቀባይነት ያገኘ ነው። አለቃ አያሌው ታምሩ እነዚህ ግጥሞች የባለመልክኡን መልክ ከስሙ በመጀመር ከራስ ጸጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ድረስ በቅደም ተከተል በስንኝ የሚያመሰግኑ ናቸው /1992/ ይላሉ። እንደ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የአለቃ አያሌውም ፍቺ የመልክእን ዋና ዋና ባሕርያት ማለት ገላጭ መሆኑን፣ የሰውነት አካላትን መዘርዘሩን፣ ምስጋና መሆኑንና በስንኝ መጻፉን ይጠቅሳሉ። በነዚህ ሁለት ፍቺዎች መካከል ያለውን ልዩነት የመልክእን የምስጋና መጀመሪያ ክፍል በመጥቀስና ባለመጥቀስ ነው።

ፖላንዳዊው ምሁር አሌክሳንደር ፌሬንክ /1985፣ 283/ መልክእን ሲፈታው «የባለ መልክኡን» የተለየዩ የሰውነት አካላት በአብዛኛው ከራስ ጀምሮ እስከ እግር ድረስ የሚያመሰግን ገላጭ ግጥም ነው ይላል። ይህ የፌሬንክ ፍቺም ከላይ ከጠቀስናቸው የቤተ ክህነት ሊቃውንት ፍቺዎች ጋር የተመሳሰለ ነው፤ ከጥቂት ልዩነቶች በቀር። ፌሬንክ መልክእ የሚጀምረው ከራስ ነው በማለት ስምንና ፀጉርን ሳይጠቅስ ያልፋቸዋል። ሌላው ሀርደን /1926፤29/ የተባለ ምሁር «መልክእ የእያንዳንዱን ቅዱስ የሰውነት አካል እየዘረዘረ በአንዳንድ አርኬ የማያመሰግንበት መዝሙር ነው» ይላል። ይህ ፍቺ የሰውነት አካላት በቅደም ተከተል ስለመመስገናቸው አይናገርም። እርግጥ ብዙ አርኬዎተ ያሉት መሆኑን ይጠቅሳል፤ አንድ አርኬ ለአንድ የሰውነት ክፍል በማለት ቢሳሳትም በተጨማሪም መልክእ የሚጻፍላቸው ቅዱሳን ብቻ እንደሆኑ ያስመስላል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የመልክእ ፍቺዎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ባለመልክኦቹ የተለየዩ ብልቶች ያላቸው ግዙፍ አካል እንደሆኑ ይጠቅሳሉ። ግዙፍ አካላት የሌላቸው መልክእ የተጻፈላቸው አሉ። ከእነዚህ ግዙፍ አካል ሳይኖራቸው መልክእ ከተጻፈላቸው ውስጥ ንዋያተ ቅድሳት፣ የጸሎት መሕፍትና ልዑል እግዚአብሔር ይገኙበታል። ለምሳሌ ያህል ጠቢበ ጠቢባንን፣ መልክአ መስቀልን፣ መልክአ ስንበትን መልክአ አንቀጸ ብርሃንን መጥቀስ ይቻላል። ስለዚህ መልክእ ማለት የባለመኩልን የሰውነት አካላት እና ወይም ሌሎች ነገሮችን በማመስገን ምሕረትን የሚለምን ባሉብዙ አርኬዎች የምስጋና ግጥም ነው።

## 1.2 መልክአ መልክእ

### የተጀመረበትና የቆመበት ዘመን

መልክእ መጻፍ የተጀመረበትን ጊዜ በእርግጠኛነት መናገር አይቻልም። እኔ እስከማወቀው ድረስም ይህንኑ በእርግጠኛነት የተናገረ ተመራማሪም የለም።

መልክእ መደረስ የጀመሩበትን ሳይሆን በስፋት የተጻፉበትን ዘመን 17ኛው ምእተ ዓመት የሚያደርጉ አሉ። /ፌሬንክ፣ 1985፣ 285/። ዓለማየሁ ሞገስ /1952፣4/ ወደ 14ኛው ምእተ ዓመት ይወስዱታል። እንደ ፔደርሰን /1989፣557/ያለት ደግሞ መልክእ እስከ 17ኛ ምእተ ዓመት ድረስ እንዳልተጀመረ ይናገራሉ። የዚህ ሁሉ ልዩነት መነሻው ድርሰቶቹ በተጻፉበት ብራና ላይ ጊዜን የሚጠቁም ምንም ነገር አለመገኘቱ ነው። «እግዚአብሐር መልክ አለው ወይስ የለውም» የሚለው ጉዳይ በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ጊዜ ያወዛገበ ነገር ነበር። /ሩንግሬን፣ 1982፣59/። ደቀ እስጢፋ የተባሉ የድንግል ማርያምን የመላእክትን፣ የቅዱሳንንና የጻድቃንን

ከእግዚአብሔር የማማለድ ጉዳይን ያልተቀበሉት በዚያው ዘመን የተነሱ ነበሩ። እነዚሁ ሰዎች ለቅዱሳንና ለሥዕለ አድኅኖ ክብር የሚሰጠውን ስግደትም ይቃወሙ ነበር። ይህ የደቀ እስጢፎ እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያን ኑፋቄ ነው ተብሎ በንጉሡ ፍርድ የከፋ ቅጣት ተፈጸሞባቸዋል።

ይህ ውዝግብ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትን የምልጃን ኃይልና ለቅዱሳንና ለሥእሎቻቸው መስገድን የሚያረጋግጡበትን አዲስ የግእዝ ግጥም ስልት እንዲያስገኙ ግፊት የሆናቸው ይመስላል። ይህ መላምት እውነት የሚመስለው በዚያ ዘመን ይህን ኑፋቄ የሚቃወሙ ብዙ ሃይማኖታዊ ጽሑፎች በመውጣታቸው ነው። የሚከተለው አርኬ የዚህን ኑፋቄ ችግር ያነሳል። ሰላም ሰላም ለመልክአ ሥዕልኪ ኩሉ እምነ ፀሐይ ወወርኅ ዘያበርህ ሥነ ፀዳሉ ወበእንተዝ ማርያም ሰብአ ቤትኪ ዳበሉ ስብሐት ወክብር ወስጊድ ለመንግሥት ይደሉ ማርያም በረከትኪ ምስሌነ ይሀሉ። /መልክአ ሥዕል፣ አርኬ 23/

ይህ አርኬ ለቅድስት ድንግል ማርያም መስገድ ተገቢ መሆኑን ይናገራል። የሚከተሉም ስንኝ ይህንኑ ኑፋቄ በቀጥታ ያወግዛል።
ሰላም ለማርያም ዐጽፈ ወልድ ዋሕድ
ወመንበረ ሕያው ነድ
ለድንግልና ይደሉ ሰጊድ
ለማርያም ዘይቤ ኢይሰግድ
ሞጸፈ መብረቅ በሊን በርእሱ ለይረድ
/መልክአ ሥዕለ ዳግሚት፣ አርኬ1/
ከዚህ በላይ ጠቀስኳቸው ሁለት አርኬዎች የስግደትን ተገቢነትና ስግደትን መቃወም ኑፋቄ እንደሆነ የሚያስረዱ ናቸው።

ሌላው ይህን መላምት የሚደግፈው በየገድላቱ መጨረሻ ወይም መጀመሪያ መልክእን መጨመር ልማድ መሆኑ ነው። ገድላት በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት መጻፍ እንደተጀመረ ይነገራል። /አምሳሉ፣ 1976፣54/። ስለዚህ መልክእም በዚያው ጊዜ መገጠም ጀምሮ ሊሆን ይችላል። የሆነው ሆኖ ይህ ጉዳይ የብራናዎቹን ጥቅል ጥናት የማሻና የባመልክቱን ታሪክ ማጥናትን የሚጠይቅ ምርምር መስክ ነው።

## 1.3 ደራሲ

የሁሉም መልክእ መልክእ ደራሲዎች /በአብዛኛው/ አይታወቁም። እያንዳንዱ የመልክእ ደራሲ በድርሰቱ ውስጥ የራሱን የተለየ የአጻጻፍ ስልት ስለማይጠቀም ይህ ጉዳይ ብዙም ችግር አይሆንም የሥነ ቃል ደራሲው አይታወቅም፣ ደራሲያቸውን ለመለየት ያስቸገሩ ብዙ ድርሰቶችም በዓለማችን ይገኛሉ፤ ነገር ግን መልክእን ልዩ የሚያደርገው ደራሲዎቹ የራሳቸውን ልዩ ስልት ሳይጠቀሙ ራሳቸውን ሆን ብለው ያልጠቀሱ በመሆናቸው ነው።

የመልክእ መልክእ ደራሲያን እንደ ባለቅኔዎች አካባቢን በመከታተልና በምናብ ምጥቀት አይታወቁም። /አያሌው፣ 1992/። እንደ ተማረና ጥሩ መናገር /መጻፍ/ እንደሚችል ሰው እንጂ። የመልክእ ክብሩ በደራሲው ታላቅነት ሳይሆን በባለመልክኡ ታላቅነት ነው። በመልክእ ውስጥ የሠፈሩት የአንድ ሰው ስሜትን የያዙ ሳይሆኑ ለሁሉም ሰው የሚሆኑ ምስጋና፣ ኑዛዜ፣ ምሕረትና ልመናን የያዙ ናቸው።

የመልክአ መልክእ ደራስያን የአጻጻፍ ልማድን ተከትለው የሚጽፉ ናቸው። ደራስያኑ የሚጽፉበት ርእስ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የአጻጻፍ ስልቱም የሚይዙት ስሜትም ተወስኖ የተሰጣቸው ነው። አንድ ጊዜ የአጻጻፍ ስልቱ ካደገ በኋላ የመልክእ ቅጹ እንደ ሕግ ተይዞ ተከታዮች እንዲከተሉት ሆኗል። ስለዚህም ግላዊ የሆነው ስሜታቸው በሚጽፉት መልክእ ውስጥ ሊገለጽ አይችልም። ዋና ጉዳያቸው ያጻጻፍ ሥርዓቱን ተከተለው መጻፍ ነው። በአጠቃላይ መልክእ መልክእ ግልጽ የአጻጻፍ ስልት ያለው የአካላት ገለጻ ነው። ስለዚህም ሊነበቡ የሚገባቸው በማስተዋል ነው።

መልክእ መልክእ ለጸሎትነት የሚያገለግል ግጥሞች ናቸው። ምሕረትን የሚለምኑትም ደራሲዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ጸሎተኛው ራሱን በደራሲው ቦታ ተክቶ እኔ እያለ ይናገራል። ይህ ራስን በደራሲው ቦታ ማስቀመጥ ደራሲውን ከአንባቢው አእምሮ ያርቀዋል።

ይህም ጸሎተኛው የሚያቀርበውን የምስጋናና የልመና ጸሎት የራሱ አድርጐ እንዲቆጥር ያደርገዋል:: ይህን የሚያስረዳ ምሳሌ ልስጥ::

ማኅበረ ምእመናን ወምእመናት
እስኪያክ ተአመኀ
ለነሚአ ሥጋከ ወትረ ነበ ተፀየኀ
ወልደ አብ ክርስቶስ ዘኢትትፈለጥ እመ ሕፅኀ
እስብክ ሎሙ ሕማመመከ ወመስቀልከ አዜኀ
ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ሊተ እምሰማይ ፌኑ:: /መልክአ ቁርባን፣ አርኬ1/

ይህ ግጥም የሚደረመው በካህናት ሲሆን ካህኑ ሁሉ ራሱን በደራሲው ቦታ እንዲተካ የሚያደርግ ነው::

## 1.4 ባለመልክአ

ባለመልክአቹን በሚያመለክት እስካሁን የተጻፉት መልክአ መልክእ በአራት ይከፈላሉ::

ሀ) እግዚአብሔር

ለእግዚአብሔር /ሥላሴ/ የተጻፉ መልክአ መልክእ አሉ:: ለምሳሌ መልክአ እግዚአብሔ አብ፣ ጠቢብ ጠቢባን፣ መልክአ ጰራቅሊጦስና መልክአ ሥላሴ ይጠቀሳሉ::

ለ) መላእክት

ለመላእክት የተጻፉ ብዙ መልክአ አሉ:: እነዚህን ለሁለት መክፈል እንችላለን በውል ስም የተጻፉና ለእኔ ባይ የተጻፉ:: የወል ስም ለተሰጣቸው መላእክት የተጻፉ እንደ መልክአ ዑቃቤ መልአክ እና መልአክ መላአክት ያሉ፣ እኔ ባይ ለሆኑ የተጸውኦ ስም ላላቸው መላእክትም በስማቸው መልክአ መልክእ የተደረሰላቸው ሲሆን ለምሳሌም መልክአ ሚካኤልንና መልክአ ገብርኤልን መጥቀስ ይቻላል::

ሐ) የሰው ልጆች

ለቅዱሳን፣ ለሰማታትና ለጻድቃን የተጻፉ ብዙ መልክአ አሉ:: እነዚህንም እንደላይኛው ለሁለት መክፈል እንችላለን:: የወል ስም ያላቸው እነደ መልክአ ሰማዕታት፣ መልክአ ነቢያት፣ መልክአ ጻድቃን መልክአ ሰለስቱ ምእትና የመሳሰሉት ናቸው:: እኔ ይ የተጸውኦ ስም ለተሰጣቸው የተጻፉ አሉ፣ መልክአ ጊዮርጊስ፣ መልክአ አዳም፣ ከዚህም በተጨማሪ በቤተ ክርስቲያን ጻድቅ ናቸው ተብለው ላልተከበሩ ነገሥታትም መልክአ ተደርሶላቸዋል:: መልክአ አፄ ቴዎድሮስ፣ መልክአ አፄ ዮሐንስ፣ መልክአ አፄ ምኒልክና የመሳሰሉት::

ሀ) ረቂቅና ሕያው ያልሆኑ

ለረቂቅ ሐሳቦችና ሕያው ላልሆኑ ግዑዝ ነገሮች መልክአ መልክእ ተጽፎ እናገኛለን:: ረቂቅ ሐሳቦች ማለት እንደ ፍቅር፣ ባሕርይና ጠባይ ሲሆኑ ለነዚህ መልክአ ፍቅር፣ መልክአ ባሕርይ፣ መልክአ ጠባይ መልክአ ሰንበት የሚሉ መልክአ ተጽፈውላቸዋል:: ሕያው ያልሆኑ ነገሮች ያልኳቸውም ንዋያተ ቅዱሳት የጸሎት መጻሕፍትና የመሳሰሉት ሲሆኑ በዚህ ክፍል መልክአ አንቀጸ ብርሃን፣ መልክአ ሥዕልና መልክአ ቤተ ክርስቲያንን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል::

አንዳንድ ባለመልክአ ግዙፍ አካልና ሰብአዊ መልክአ ባይኖራቸውም እንዳላቸው ተደርጐ በሰውኛ ተጽፎላቸዋል:: ለምሳሌ መልክአ ቤተ ክርስቲያን፣ መልክአ ፍቅር እና መልክአ ሰንበት ሰብአዊ አካል እንዳላቸው ተደርጐ ተጽፎላቸዋል:: በቤተ ክርስቲያን በልዩ ክብር የሚታዩ አንዳንድ ባለመልክአ መልክእ በስማቸው የተለያዩ ብዙ መልክአ ተደርሶላቸዋል:: ለምሳሌ የባለመልክኡን ልዩ በዓላት በማሰብ መልክአ ይጻፋል:: ለምሳሌ ለኢየሱስ ክርስቶስና ለድንግል ማርያም የተደረሱትን እንመልከት::

## 1.5 መልክአ መልክእና ቅዳሴ

| ተ.ቁ | ለኢየሱስ ክርስቶስ | ተ.ቁ | ለድንግል ማርያም |
|---|---|---|---|
| 1 | መልክአ ኢየሱስ | 1 | መልክአ ማርያም |
| 2 | መልክአ ዐማኑኤል | 2 | መልክአ ኤዶም |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3 | መልክአ መድኃኒዓለም | 3 | መልክአ ፍልሰታ ለማርያም |
| 4 | መልክአ መድኃኔዓለም እሰግድ | 4 | መልክአ ቁስቋም |
| 5 | መልክአ ቁርባን | 5 | መልክአ ሥዕል |
| 6 | መልክአ መስቀል | 6 | መልክአ ኪዳነ ምህረት |
| 7 | ልሳነ ሰብእ | 7 | መልክአ ልደታ ለማርያም |
| 8 | መልክአ ቅንዋት | 8 | መልክአ ልደታ ለማርያም ዳግማዊት |
| 9 | መልክአ ማኅያዊ | 9 | መልክአ ማርያም ካልእ |
| | | 10 | መልክአ ማርያም ሣልሲት |
| | | 11 | መልክአ ድንግል |
| | | 12 | መልክአ ጎልጎታ |
| | | 13 | መልክአ በአታ |

ቅዳሴ መሥዋዕት፣ ጸሎትና የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት የሚከናወኑበት ሥርዓት ጸሎት ነው:: ሥጋ ወደሙን ካህናት ጸሎት ነው:: ሥጋ ወደሙን ካህናት ለምእመናን ከማቀበላቸው በፊትና በኋላ መልክአ ቁርባንን ይዘምሩታል:: መልክአ ቁርባን የክርስቶስን ሥጋና ደም የማያከብር መልክእ ነው::

ከቅዳሴ በኋላ በየዕለቱ ከሚደረገሙ ጸሎታት ውስጥ ከውዳሴ ማርያም ጋር የማጸለዩት መልክአ ማርያምና መልክአ ኢየሱስ ይገኘ ብታል፤ እነዚህ መልክአ በካህናቱ ይደገማሉ:: ይህ ጸሎት የሚካሄደው መልክኡ እስኪፈጸም ድረስ በቅደም ተከተሉ ለካህናቱና ለሊቃውንቱ አንዳንድ አርኬ በማደል ነው:: ማደሉ የሚካሄደው በዲያቆናት ወይም በሌሎች የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሲሆን የሚጠቀሱት እያንዳንዱ አርኬ የሚያስመሰገኑትን የመጀመያውን የሰውነት አካል ወይም ሌላ ቃል ነው:: ከዚህ በተጨማሪም ዕለቱ መታሰቢያው የሆነ ጻድቅ፣ ሰማዕታት መልአክ ወይም ሌላ በዕለቱ ከተጠቀሱት መልክእ በተጨማሪ የእርሱ መልክእም ይደገማል:: ቤተ ክርስቲያኑ የሚታሰብበትን ስም የያዘው መልክእ ወይም ጻድቅ ስምም በዚያ ቤተ ክርስቲያን መልክኡ በየዕለቱ ይደገማል:: ለምሳሌ በላሊበላ መልክአ ላሊበላ እና በሳማ ሰንበት ደግሞ መልክአ ሰንበት በየቀኑ ይደገማሉ::
መልክእ በዜማ ሊዘመሩ ይችላሉ:: የሚዘምሩትም ከመልክኡ ውስጥ ተመርጠው የወጡ ጥቂት ስንኞች ናቸው:: የሚከበረው ዕለት የሚታሰብበት መልክእ ወይም ጻድቅ.. በዓመታዊ ክብሩ ዕለት የሚታሰብበት መልክእ ወይም ጻድቅ.. በዓመታዊ ክብሩ ዕለት ከመልአኩ ውስጥ ጥቂት ስንኞች ተመርጠው በጸናጽል፣ በከበሮ ይዘመራል:: ለምሳሌ ለልደት በዓል ከመልክአ ኢየሱስ ሁለት አርኬዎች ይዘመራሉ፤ አርኬ 1 እና አርኬ 28::

መልክእ እንደ ጸሎት መጽሐፍ ከማገልገሉም በተጨማሪ የማስተማር ተግባርንም ያከናውናል:: የባለመልክኡን ሕይወትና ተአምራት ከጸሎተኛው ጋር ያስተዋውቃል:: ይህን የሚያደርገውም መልክኡ የተመሰረተው በባለመልክኡ ታሪክ ላይ በመሆኑ ነው፡ ስለዚህም መልክእ ለመረዳት የባለ መልክኡን ታሪክና ትምህርት ሃይማኖት ማወቅ አስፈላጊ ነው፡
ሰላም ለዝክረ ስምከ ለመሐላ ዘኢይሔሱ ዘአንበረ ቅድመ እግዚአብሔር በአትሮንሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዳዊት ባሕርየ ክርሱ አክሊለ ስምከ እንዘ ይቀቀጸል በርእሱ አህጉረ ጸ ወረሲ ኢያሱ /መልክአ ኢየሱስ አርኬ 1/
ይህን አርኬ ለመረዳት የመስፍኑ እስራኤል ኢያሱን ታሪክ፣ የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ትውልድና መሥጢር ሥጋዌ ማወቅ ያሻል:: የኢየሱስና የኢያሱን የስም አንድነት ማወቅም አስፈላጊ ነው:: ኢያሱ የተስፋይቱን ምድር የመውረስ ታሪክና የጌታችንን ከዳዊት ዘር መወለድንም ማወቅ አስፈላጊ ነው:: እያንዳንዱ እንደየ ወቅቱ መጤን የዚህን አርኬ ትርጓሜ እያለፉና ጥልቀት እየሰጠ መቀጠል ይችላል::

**1. አነስተኛነት /Prosody/**

አነስተኛነት ያልኩት የግጥሙን ውጫዊ ገጽታ የሚያሳዩትን ቤት ምትና አርኬን ነው::

2.1 ቤት

መመልክአ የስንኞቹ የመጨረሻ ቤት መምቻ ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ሆሄ ነው:: መልክአ ሁልጊዜም በአንድ ዓይነት ሆሄ ቤት የሚመቱ ባለ አምስት ስንኝ አርኬዎች ያሏቸው ናቸው:: ሰላም ለአዕይንቲከ ከመ ምሉዕ ምዕቃለ ማይ
አለ ይትረአይ ወትረ በመንበረ መጽሔት ርሱይ /ያጌጠ/
ኢየሱስ ክርስቶስ መስተሥርየ ኩሉ ጌጋዩ ንዝኃኒ እግዚኦ በእዛብከ ሠናይ
ወአጸዕድወኒ እመ በረድ ጽሩይ /መልክአ ኢየሱስ፣ አርኬ 6/
ከዚህ በላይ በተጠቀሰው አርኬ ውስጥ ያሉት 5 ስንኞተ ቤት የሚመቱ «ይ» በተባለው ሆሄ ነው:: የዚህ ቤት መምታት ፋይዳ ስንኞቹ ቤሚዜሙበት ጊዜ የዜማው አካሄድ እንዲጠበቅ ይዳርጋሉ::

2.2 ምት /ቀለም/

ዓለማየሁ ሞገስ /1969/ የግእዝ ሥነ ግጥምን አስነኛነት ሲያብራሩ የግእዝን ሥነ ግጥም ዜማ የሚወስኑት የሚቆሩ ድምፆች /ሆሄያት/ እና የአነባብ ሥርዓት /ተነሽ፣ ውዳቂ፣ ሰያፍ/ ናቸው:: እንደ አቶ ዓለማየሁ ሞገስ ጥናት በአንድ አርኬ ውስጥ የሚገኙ ስንኞች የተለያዩ መጠን /የቀለም/ ያላቸው ከዚህም ሌላ የመጀመሪያው አርኬ ስንኞች ቀለም ከተከታዩ አርኬ ስንኞች እኩል ሆነው የማሄዱ አይደሉም:: ይህም አሰልቺነትን ያስወግዳል::

/መልክአ ኢየሱስ አርኬ 4/

በመልክአ አንድ ዓይነነት የማይቀያየር ወጥ ዜማ የሌለው በባለ አምስት ስንኝ አርኬ ውስጥ አንድ አይነት ወጥ ምት ባለመኖሩ ነው:: በአጠቃላይ መልክአ ቁርጥ ያለ የምት ቀመር የሌለው ሲሆን ዜማዊ ነው::

2.3 አርኬ

| | |
|---|---|
| ሰላም ለመልክእኪ ዘተሠርገው አሚረ | 6..........ሀ |
| በያ በርሀ ወትረ | 7..........ለ |
| ፍቅርቅየ አንቲ አንተ ታበድሪ ፍቅረ | 14.........ለ |
| አርእይኒ ገጸ ዚአኪ ማርየም ምዕረ | 16.........ሀ |
| ዘኢይሰምዕ ካልዕ እንግረኪ ነገረ | 14.........ለ |
| /መልአከእ ማርያም አርኬ 51/ | |
| ሰላም ለገጽከ አምሥነ ኩርያሬስ ስቡሕ | 15.........ሀ |
| ወፍሡሕ ከመወርኅ ዘእሜ ገዛሀ | 12.........ለ |
| ኢየሱስ ክርስቶስ ታቦት ሕይወቱ ለኖኅ | 12.........ለ |
| ኅበአኒ እግዚኦ በውሳጤከ ስፋሕ | 12.........ለ |
| ማየ ኩነኔ አመ ዘዓመ አይኅ /ጥፋት፤ | |
| የጥፋት ውኃ/ | 12.........ለ |

መልክአ በአርኬዎች የተከፋፈሉ ግጥሞች ናቸው:: እያንዳንዱ አርኬ አምስት አምስት ስንኞች አሉት:: ባለአምስት ስንኝ አርኬዎች በሌሎችም የግእዝ የግጥም ዓይነቶች ውስጥ የተለመደ ነው:: ለአምስት ስንኝ አርኬ ከሚጠቀሙት ውስጥ የስንክሳር አርኬዎች፣ ቅኔ ሰዓታት፣ ማኅሌተ ጽጌና ሰቆቃው ድንግል ሊጠቀሱ ይችላሉ:: ሰቆቃው ድንግል አንዳንድ ጊዜ ባለ ስድስት ስንኝ አርኬም ይጠቀማል::

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱት አርኬዎች በሙሉ ይህንን የሚያስረዱ ናቸው:: ለምሳሌ ግን የሚከተለውን አርኬ እንመልከት::

| | |
|---|---|
| ሰላም ለፍልሰታ ሥጋከ ለዘርዐ ያዕቀብ | /1/ |
| ወሊቀ ካህናት ገብርኤል በሐዘለከ መዓልተ | /2/ |
| ዜና ማርቆስ ያዕቆብ ፈውሶተ ድውይ ሐውልተ /3/ | |
| አቅሞ በቅድሜያ አንዝ ታስተበቁዕ አንተ | /4/ |
| ኅበ አምላክከ ሰማያዊ ለቤዛ ዘመተ:: | /5/ |

/መልክአ ዘና ማርቆስ አርኬ 48/

በብዙ መልክአ አርኬዎች የመጀመሪያ ስንኝ ላይ የሚገኘው መነሻ ቃል ሰላም ነው:: ታትመው ካገኘኋቸው 50 መልክአ ውስጥ የአርባ አንድ መልክአ አርኬዎች የመነሻ ቃል ሰላም ነው:: ተማኅፀንኩ የሁለት መልክአ «አ» «ንኢ» የአንዳንድ መልክአ አርኬዎች መነሻ ቃላት ሲሆኑ የሦስት መልክአ አርኬዎች መነሻ ቃል ያላቸውም:: በአጠቃላይ ሲታይ ሰላም የመልክአ አርኬዎች መነሻ ቃል ነው::

በመልክአ አርኬዎች ውስጥ ከመነሻ ቃል ቀጥሎ የሚመሰገነው የባለ መልክኡ የአካል ስም ወይም ሌላ ነገር ይከተላለል:: ካየኋቸው 50 መልክአ መልክአ ውስጥ አርባ አንዱ የየባለመልክኡን የሰውነት ክፍሎች እየዘረዘሩ የሚያመሰግኑ ናቸው:: አራቱ የየባለመልክኡን ተግባራትና አንዳንድ ሁነቶችን አራቱ ደግሞ ምንም የተለየ የሚዘረዝሩት ነገር የለም:: የቀሩት ሁለቱ መልክአንና የተጻፉት ለጸሎት መጻሕፍት ነው ለውዳሴ ማርያምና ለአንቀጸ ብርሃን የነዚህ ሁለት መልክአ አርኬዎች መነሻ ቃል ነው: ለምሳሌ «የመልክአ አንቀጽ ብርሃን» የመጀመሪያዎቹ ሦስት አርኬዎችና የአንቀጸ ብርሃን የመጀመሪያዎቹ ሦስት አንቀጽ መነሻ ቃላት ቅድስት አሥርቱ እና ቀዲሙ ናቸው::

የየባለመልክኡን የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች የማይዘረዝሩና የማያመሰግኑ ነገር ግን የባለመልክኡን መለያ ሁኔታ የሚናገሩ አንዳንድ መልክአ አሉ:: ለምሳሌ በብራና ላይ ተጽፎ በጀመደ ማርያም ገዳም ያገኘሁት መልክአ ልደታ ከአርኬዎች ሁሉ በመነሻ ሐረግነት የተጠቀመው «ሰላም ለልደትኪ...» የሚለውን ነው:: የታተመው «መልክአ ልደታ ለማርያም» የድንግል ማርያምን የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች እየዘረዘረ የሚያመሰግን ቢሆንም ልደቱን ካሉት 31 አርኬዎች ውስጥ በሃያ ዘጠኙ ይጠቅሰዋል:: በተመሳሳይ ሁኔታ «በመልክአ ፍልሰታ ለማርያም» ውስጥ የትንሣኤዋንና የሥጋዋን ዕርገት ከሚያመሰግኑት መጨረሻዎቹ ሁለት አርኬዎች በስተቀር የሁሉም አርኬዎች መነሻ ሐረግ «ሰላም ለፍልሰታ ሥጋኪ» ነው::

መልክኡ የተደረሰለት ግዑዝ ነገር ወይም የተቀደሱ ዕለታት ሰዋዊ ባሕርይ ተሰጥቷቸው ልዩ ልዩ የሰውነት ክፍሎች እንዳላቸው ተደርገዋል:: ለምሳሌ ሰንበትን ብንወስድ በመልክአ ሰንበት ውስጥ የሰውነት ክፍሎች ተዘርዝረው ሲያመሰግኑ እናያለን::

ሰላም ለከናፍርኪ ዘነበበ በሁባሬ
እንበለ ድማሬ
ሰንበተ ክርስቲያን ቅድስት ሙዳየ ምጽዋት ዘቤተ ኀሬ
እሰዕለኪ እግዝእትየ እስመ አቅረብኩ ዝማሬ
ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ሉተ ጸግወኒ ፍሬ /መልክአ ሰንበት፣ አርኬ 10/

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው አርኬ የተመሰገነው የሰነውነት ክፍል ከንፈር ነው፣ ነገር ግን ሰዋዊ ባሕርይ ካልተሰጠው በቀር ዕለት ከንፈር የለውም:: ግዕዝና ረቂቅ ሐሳቦችን ሰዋዊ ባሕርይ ሰጥቶ ማመስገን እንደ አንድ ባሕርይ የሚቆጠር ነው::

መልክአ በአንደኛ መደብ የተተፉ ሲሆን ባለመልክአ መልክኡ ደግሞ በሁለተኛ መደብ የሚጠሩበት ግጥም ነው:: በተጨማሪም ደራሲው ወይም መልክኡን ደጋሚው በአንደኛ መደብ ባለመልክኡ ደግሞ በሁለተኛ መደብ ሆነው በቀጥታ እንደሚነጋገሩ ሆኖ በመጻፍ የልመናና ምልጃ መቅረቢያም ነው::

በየመልክአ መልክኡ ውስጥ በቋሚነት የሚገኘው እኔ የሚለው ተውላጠ ስም በደራሲው ወይም በደጋሚውና በባለመልክኡ መሐል መንፈሳዊ መቀራረብን መፍጠሪያ መንገድ ነው:: እኔ የሚለው ተውላጠ ስም ጸሎተኛውን ወይም ልመና አቅራቢወን በመልክኡ ደራሲ ቦታ ራሱን እንዲያስቀምጥ አድርጎ በእሱ /እሷ/ እና በባለመልክኡ መካከል ግላዊና ቀጥተኛ ግንኙነት ፈጥሮ ለባለመልክኡ ልመናውን እንዲያቀርብና ኃጢአቱን እንዲናገር አስችሏል:: ይህ ራስን በመልክኡ ደራሲ ቦታ መተካት

አንድ ቦታ ችግር ሲገጥመው እናያለን:: ልሳነ ሰብእ ውስጥ ያለው እኔ ባይ በአንደበቱ 50 ዓመታት እንደተገዛ/ እንደተመራ/ ይናገራል:: ይህ ግላዊ የሆነ የአንድ ሰው /ምናልባት የመልክኡ ደራሲ/ ዕድሜ ቁጥር ከ50 ዓመት በታች የሆኑትን የመልክኡ ደጋሚዎች በደራሲው ቦታ ራሳቸውን እንዲያስቀምጡ ያደርጋቸዋል:: ረዥሙ ጠቢበ ጠቢባን ሲሆን 102 አርኬዎች ይዟል:: በጣም አጭሩ ደግሞ «መልክአ ዑቃቤ መልአክ» ሲሆን ባለ 14 አርኬዎች ነው::

### 3. ዘይቤ /ምሳሌ/

ዘይቤ የሥነ ግጥም ዋነኛ መሣሪያ ነው:: ለቅኔያዊ ፍች፣ ለሥነ ግጥማዊ ቅርጽና ለውበቱም ዋነኛ ጠቋሚ ነው:: ዘይቤን እዚህ የምንጠቀምበት በመልክአ መልክአ ውስጥ የገቡ ምስሎችን /ዘይቤያዊ አነጋገሮችን/ ወክሎ ነው:: መልክአ የባለመልክኡን አካላዊ ክፍሎች የሚገልጥ ነው:: የመልክአ መልክእን ዘይቤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነና ያልሆነ ብለን ለሁለት መክፈል እንችላለን:: ሁለቱንም የዘይቤ ዓይነቶች ጥቂት ምሳሌዎችን በመጥቀስ ለማስረዳት እሞክራለሁ::

### 3.1 መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘይቤ

በመልክአ ውስጥ ካሉት ዘይቤዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱት በቁጥር ከሌሎች የዘይቤ ዓይነቶች በጣም ይበልጣሉ:: ከብሉይና ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተወሰዱ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ለተራው አንባቢ የማይታወቁ ነገሮችም ተጠቁመው ይገኛሉ:: ለምሳሌ:- ማርያም ኅትምት መጽሐፈ ዮሐንስ ነቢየ /3/ ልክዒ በላዕሌየ ለፊደልኪ ማኅተሞ /4/ ከመ ኢይርአየኒ ዓይነ ሞት በስሙ መጻሕሞ /5/ /መልክአ ማርያም መጥልሲ፣ አርኬ 3፣ ስንኝ 3-5/ ሦስተኛው ስንኝ ድንግል ማርያምን ከዮሐንስ ራእይ በተወሰደ ጥቆምታ ይገልጸታል:: በዮሐንስ ራእይ እንደተጻፈው ቅዱስ ዮሐንስ በሰባት ማኅተም የታተመ መጽሐፍ ያያል:: ይህ መጽሐፍ የክርስቶስ ምሳሌ በሆነ በበጉ ካልሆነ በቀር የሚከፈት አይደለም:: /ራእይ 5፤1/:: በዚህ ስንኝ ውስጥ በማኅተም የተዘጋው መጽሐፍ ድንግል ማርያምን የሚገልጽ ሲሆን /መጻሕፍተ ሐዲሳት ሠለስቱ፣ 1989÷382/ ማኅተሙ ደግሞ ድንግልናዋን ይገልጻል:: በዮሐንስ ራእይ ውስጥ ያለው በግ መጥምቁ ዮሐንስን «እነሆ የእግዚአብሔር በግ» /ዮሐ 1÷29/ ሲል እንደ መሰከረ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው:: በዮሐንስ ራእይ መጽሐፉን የሚከፍተው በጉ እንደሆነ ከድንግል ማርያም በድንግልና የተወለደው ኢየሱስ መሆኑን ያስረዳል::

ከ «መልክአ ገብርኤል» ሌላ ምሳሌ ልጥቀስ:-

እግዚአብሔር ሀበኒ ሲሳየ ልቡና መጽሐፈ
ወአፉየ መሴ ለእመ ኮነ ደያፈ
ጸራቅሊጦስ አሮን ይኩነኒ አፈ::
/መልክአ ገብርኤል አርኬ1፣ ስንኝ 3-5/

በአራተኛውን በአምስተኛው ስንኞች ውስጥ ሊቀ ነቢያት ሙሴና ካህኑ አሮን ተጠቅሰዋል:: በኦሪት ዘጸአት እንደተጠቀሰው ሙሴ አንደበቱ ኮልታፋ ነበር /ጸዘ 4÷10/ ስለዚህም እግዚአብሔር አሮንን የሙሴ አንደበት አደረገለት /ዘጸ. 4÷14-15/:: ይህን ታሪክ በመጠቆም ደራሲው እግዚአብሔር መፅሐፈ ቅዱስ «ጳራቅሊጦስ»ን አንደበት አድርጐ እንዲልክለት ይለምናል:: ሙሴ የደራሲውን አሳምሮ መናገር አለመቻል አሮን ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን ለሰዎች አንደበት መሆን ይገልጻል:: ዘይቤው ትይዩ (Symmetrical) ነው፤ ሙሴና አሮን ለአንደበተ ኮልታፋነትና ለጰራቅሊጦስ ቆመዋልና::

አንድ ምሳሌ መጨመር ነገሩን የበለጠ ሊያብራራው ይችላል::

ልብሰ ሰማዕትና ይኩነኒ ምሕረትክሙ ክዳነ
ላዕሌየ እስመ ኢሀሉ ልብሰ አስጢፋኖስ እብን
ወሥጋዊሁ እሳት ለቂርቆስ ሕፃን::
/መልክአ ሥላሴ፣ አርኬ 37፣ ስንኝ 3-5/

ከ4ኛውና 5ኛው ስንኝ ውስጥ «የእስጢፋኖስ ልብሰ ድንጋይ» እና «የቂርቆስ ጌጥ እሳት» ጥቆምታ ሆነው ገብተዋል:: እነዚህ ጥቆምታዎች የተገኙ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሐዋርያት ሥራ፤ ከድርሳነ ሚካኤልና ከገድለ ቂርቆስ ወኢየሉጣ ነው:: እስጢፋኖስ በአይሁድ በድንጋይ ተወግሮ የተገደለው የመጀመሪያው ሰማዕት ነው /የሐዋ. 7÷54-60/:: ደራሲው ድንጋይን ለሰማዕትነት ተለዋጭ አድርጐ ተጠቅሞበታል:: እነዚህ ሁለት ስንኞች በዘይቤ የታመቁ ናቸው:: ደራሲው የሚያነሳው ልብስ በቁሙ ልብስ ሳይሆን የቅድስት ሥላሴ ምሕረት ሲሆን ራሱ ደግሞ በተራው እስጢፋኖስ በተወገረበት ድንጋይ ይገለጻል:: ያው ልብስ በእሳትም ይገለጻል፤ እሳት በተራው ደግሞ በጌጥ እንደሚገለጽ በእነዚህ ሁለት ስንኞች ውስጥ ዘይቤ በዘይቤ ላይ ተደራርቦ ይገኛል:: ቅዱስ እስጢፋኖስ የተወገረበት ድንጋይና ቅዱስ ቂርቆስ የተጣለበት እሳት በልብስና በጌጥ ተገልጸዋል፤ ሁለቱም ግን ሰማዕትነትን የሚገልጹ ናቸው::

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅምታን በብዛት በዘይቤነት መጠቀም የመልክእ መልክእ አንዱ ባሕርይ ነው፡፡ ለምሳሌ በመልክእ ማርያም አርከዎች 3ኛ ስንኝ ውስጥ ብቻ 20 መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅምታዎች ሲኖሩ በመልክእ ኢየሱስ ውስጥ ደግሞ 12 አሉ፡፡

በመልክአ ማርያም ውስጥ በአጠቃላይ ከ50 በላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቆምታዎች ይገኛሉ፡፡ መልክአ መጥልሲ 12 አርኬዎች ያሉት ሲሆን በ12ቱ አርኬዎች 3ኛ ስንኞች ውስጥ 12 መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቆምታዎች አሉ፡፡ የተጠቆሙት የመጽሐፍ ቅዱስ ባለታሪኮች 12ቱ ሐዋርያት ናቸው፡፡ የ12ቱን ሐዋርያት ተጋድሎና ድል በመጠቀም ድንግል ማርያምን ይገልጻል፡፡

መልክአ ተክለ ሃይማኖት ተመሳሳይ ሁኔታ እንደ መልክአ መጥልሲ መጽሐፍ ቅድሳዊ ጥቆምታን ተገልግሎበታል፡፡ ካሉት 57 አርኬዎች ውስጥ የ28ቱ አርኬዎች ሦስተኛ ስንኞች 24 የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችንና 24 የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችንና አራት የኋላ ዘመን የቤተ ክርስቲያንን ቅዱሳን ተለዋዋጭነት በመጠቀም ባለመልክኡን ይገልጣል፡፡ በመልክአ መጥልሲ ከመጀመሪያው ቀጥሎ ያሉት አራት አርኬዎች ሦስተኛ ስንኞች አራቱን ወንጌላውያን በወንጌላቸው ተራ በጥቆምታነት ይጠቀማል፤ ማቴዎስ፤ ማርቆስ፣ ለቃስ፣ ዮሐንስ፡፡
አንድ ምሳሌ ከመልክአ ተክለ ሃይማኖት እንጥቀስ፡-
ተክለ ሃይማኖት ለቃስ ዐቃቤ ሥራይ /መልክአ ተክለ ሃይማኖት፣ አርኬ 4፣ ስንኝ 3-5/
ይህ ስንኝ የወንጌላዊውን የሉቃስን ሐኪምነት በጥቆምታነት ይጠቁማል፡፡ ይህ ጥቆምታ የተክለ ሃይማኖትን በአማላጅነት በሽተኛ ውን የመፈወስ ኃይል ይገልጣል፡፡ የቅዱስ ሉቃስ ሐኪምነት የተገኘው ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ነው፡፡ /ቆላ. 4፥14/፡፡ የዚህ ዓይነቱ ተለዋጭ ዘይቤ በመልክአ መልክአ ውስጥ በብዛት የሚገኝ ነው፡፡ ይህም በቅዳሴ ማርያም ምዕራፍ ሦስት እና አራት ውስጥ በብዛት ያገለገለ ሲሆን ትርጓሜውን ማየት ብዙ ነገር ግልጽ ያደርጋል፡፡
ሌላው የመልክአ መልክአ ዘይቤ ባሕርይ ተመሳሳይ ገላጮችን በብዙ መልክአ ውሰጥ መጠቀም ነው፡፡ ለምሳሌ ከዋክብት፣ ጨረቃና ፀሐይ የባለመልኮቹን ፊት መገለጫ ሆነው በብዙ መልክአ መልክአ ውስጥ አገልግለዋል፡፡ ለምሳሌ መልክአ ማርያም የድንግል ማርያምን ፊት /ገጽ/ እንደሚከተለው ይገልጠዋል፡፡
ሰላም ለገጽኪ ዘጥቀይልሂ
እም ሥነ ከዋክብት ወወርኅ ወእም ሥነ ሥነ ፀሐይ መብርሂ፡፡
/መልክአ ማርያም፤ አርኬ 4፣ ስንኝ 1 እና 2/፡፡
ይህ ምስል ምናልባት ከመኃልየ መኃልይ የተወሰደ ሊሆን ይችላል፡፡
ስለዚህ በመልክአ መልክአ ወስጥ የሚያገለግሉት አንዳንድ ዘይቤዎች /በተለይ መጽሐፍ ቅዱሳዊዎቹ/ በተለያዩ መልክአ መልክአ ውስጥ በተደጋጋሚ ይገኛሉ፡፡

### 3.2 መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ዘይቤዎች

በመልክአ መልክአ ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ያልተወሰዱ ዘይቤዎች አሉ፡፡ዘይቤዎችን ደራሲዎቹ ባላቸው ምናባዊ ምጥቀት ከአካባቢያቸው ያገኟቸው ናቸው፡፡ ከመ ጽጌያት ዘገዳም ያስተጋብእ ንሕብ /መልክአ ኢየሱስ፤ አርኬ 5፣ ስንኝ 4 እና 5/፡፡ ይህ ተነጻጻሪ ዘይቤ የገባው የደራሲው/ ደጋማው የጥበብን ሁሉ ፍሬዎች በልቤ ውስጥ ሰብስብልኝ፣ የዱር አበቦች ንቦችን እንደሚሰበሰቡ ብሎ ልመናውን ለመግለጽ ነው፡፡ እዚህ ላይ ገላጩ አበባው ሳይሆን የአበባው ንብን የመሰብሰብ ኃይል ነው፡፡ ሌላው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑትን በተደጋጋሚ የሚገኙት ዘይቤዎች ምስሎች በርና መስኮት ናቸው፡፡ በነዚህ ምስሎች የሚገለጹት የሰውነት ክፍሎች አፍንጫ፣ ጆሮዎችና ከንፈሮች ናቸው፡፡ አፍንጫ በመስኮትም በበርም ወይም ባንዱ ተገልጾ ይገኛል፤ በመልክአ ኢየሱስ /አርኬ 10/፤ በመልክአ ኪዳነ ምህረት/አርኬ 10/፤በመልክአ ማርያም /አርኬ 9/ እና በመልክአ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ/አርኬ 9/፡፡
ሌላው መነሳት ያለበት ምስለ ዕንቁ ነው፡፡ የተከበሩ ማዕናት የባለመልክአ መልክእኡን ጥርስ መግለጫ ሆነው አገልግለዋል፡፡ ለምሳሌ መልክአ ኢየሱስ /አርኬ 12/ መልክአ ቁስቋም /አርኬ 4/ ና መልክአ ገብርኤል /አርኬ 9/ ውስጥ የተከበሩ ማዕድናት የባለመልክአ መልክኡን /ኢየሱስ፤ ማርየምና ገብርኤል/ ጥርስ መግለጫ ሆነው ገብተዋል፡፡ በመልክአ መልክኡ ውስጥ አገልግሎት የሰጡ የባሕር፣ ሰማያዊ አካላት /ኮከብ፣ ጨረቃ፣ ፀሐይ/ እና ሌሎች መስሎች አሉ፡፡ ሰማያዊ አከላትን በሚመለከት ከዋክብት፣

ጨረቃና ፀሐይ የአንዳንድ ባለመልክእ መልክእን ሃይማኖት ለመግለጽ አገልግለዋል:: መልክአ ገብርኤል /አርኬ 6/፣ መልክአ ተክለ ሃይማኖት /አርኬ 2/፣ መልክአ አረጋዊ /አርኬ 6/ ከዋክብትን ለዐይን መግለጫ ካደረጉት መልክአ መልክእ ውስጥ ናቸው መልክአ አረጋዊ ግን ፀሐይና ጨረቃን ነው የተጠቀመው::

### 3.3 የምስሎች አገልግሎት

በመልክእ መልክእ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የስሎቹ አገለግሎቶች ሁለት ናቸው፤ ሃይማኖታዊ እውነትን ማስተላለፍና ባለ መልክአ መልክኡን ውብ አድርጎ መግለጽ:: አንዱ የምስሎቹ አገልግሎት ሃይማኖታዊ መልክኡን ውብ አድርጐ መግለጽ:: አንዱ የመስሎቹ አገልግሉት ሃይማኖታዊ እውነትን ለልብ/ ለምናብ ሳይሆን ለአእምሮ ማስተላለፍ ነው:: የአንባቢውን ስሜት ለመያዝ አይደለም:: ለዚህ ተገቢ የሚሆኑን ምሳሌዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱት ምስሉች ናቸው:: እነዚህ ምስሎች በአብዛኛው በወኪልነት (Typological) የሚገቡ ናቸው:: በመልክአ ማርያም ውስጥ ድንግል ማርያም እንደሚከተለው ተገልጻለች::

ማርያም ድንግል ዘገዳመ ሲና ጳጦስ /አርኬ 37፣ ስንኝ 3/

የሲና ቁጥቋጦ እና ሐመልማል ተዋሕዶ /ዘጸ.1፥1-4/ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የትርጓሜ መምህራን ዘንድ ድንግል ማርያም እሳተ መለኮትን በማኅፀንዋ የመሸከምዋ ምሳሌ ነው:: /ወዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም፤ ንባቡና ትርጓሜው፣ 1983:15/:: ቁጥቋጦው የድንግል ማርያም ምሳሰ እሳቱ አለማቃጠሉ ድንግል ማርያም መለኮት ተዋሕዶ ምሳሌ ነው መሥጢረ ሥጋዌ:: ስለዚህ ገላጩ /የሲና ቁጥቋጦ/ ምክንያታዊ ዝምድና አላቸው::

ሁለተኛው የምስሎች አገልግሎት ባለመልክእ መልክኡን በመጠቀ ቋንቋ መግለጽ ነው፤ ከይዘቱ ይልቅ ወደ ቋንቋው ውበት ያደላል:: ይኼ በአብዛኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ምስሎች አገልግሎት ነው:: እንዲህ ያሉት ምስሎች ባለመልክእ መልክኡንና አንዳንድ ተጨማሪ ነገሮቹን የሚገልጡ ናቸው::

ትበከየክመ እስከ ይእዜ ቤተ ክርስቲያን ደብተራ::

ከመ ብእሲቱ ጎዝንተ ዘቀበረት በኩራ

/መልክአ ጴጥሮስ ወጳውሎስ፤ አርኬ 3፣ ስንኝ 3 እና 4/

እዚህ ላይ የበኩር ልጇን የተቀበረች ሴት ልቅሶ /ኀዘን/ ባለመልክአ መልክኡ /ጴጥሮስና ጳውሎስ/ መሥዋዕትነትን በተቀበለ ጊዜ የቤተ ክርስቲያንን ኀዘን የሚገልጽ ነው:: ስለዚህም አገልግሎቱ የቋንቋውን አጠቃቀም የመጠቀም በማድረግ ስሜቱን ማስተላለፍ ነው::

በአጠቃላይ ምስሎቹ የተለመዱ ሲሆን አገልግሎታቸውም ማስተማርና የሚገለጸውን ነገር /አሳብ/ ባማረ ቋንቋ መግለጽ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስዊ መስሎቹ ባላቸው የይዘት ተገቢነት የሚመረጡ ሲሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑት ደግሞ አንድን ነገር አጉልቶ አግዝፎ ለማሳየት በመቻላቸው ነው:: መጽሐፍ ቅድሳዊ መስሎቹ በአብዛኛው የወሰዱት ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ነው::

### ዋቢ መጻሕፍት

መልክአ ጉባኤ:- 1959 ዓ.ም አዲስ አበባ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት::
መልክአ ጉባኤ:- 1988 ዓ.ም አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት
መልክአ ጉባኤ፤ ብራና፣ ወሎ፣ ጀመደ ማርያም ገዳም::
መልክአ ልደታ ለማርያም፤ ቀን አልተጠቀሰም፣ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት
መልክአ ሥላሴ፤ 1972 ዓ.ም አዲስ አበባ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት::
መልክአ ሐዲሳት ሠለስቱ፣ ንባቡና ትርጓሜው፣ 1988 ዓ.ም አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት::
መጽሐፍ ቅዱስ፣ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣